# ሽንጋይ ፣ የሳር እባብ

ጥንትም የነበረ ፣ የጨካኞች በትር ፣ የጨካኝ አገልጋይ
እድሜውን የፈጀ ፣ ሰው ያለ ሃጢያቱ ፣ የሚያሳድድ ሰላይ
በግፍ አሳስሮ ፣ ደስታን የሚያገኝ ፣ በወገኑ ስቃይ
ጥላቻና ክፋት ፣ በውስጡ ተሞልቶ ፣ ባንደበቱ ሽንጋይ
ይሉኝታ የሌለው ፣ ከዕውነት የተጣላ ፣ ዘወትር ቃል አባይ
ህሊናውን ሸጦ ፣ ይተረተረዋል ፣ ይኸው ባደባባይ ።

የዛሬው ተረኛ ፣ ትን እስኪለው ድረስ፣ ካቅም በላይ ሲጎርስ
ምስኪኑና ደሃው ፣ በማያውቀው ነገር ፣ ደሙ እንደጎርፍ ሲፈስ
እንኳንስ ይቅርታ ፣ አንኳን የደም ካሳ ፣ እንባው አይታበስ
ጥርሱን እያሳየ ፣ ወሬ እያጣፈጠ ፣ ዘንጥሎ የሚናከስ
የግፍ ፅዋው ሞልቶ ፣ ገዳይ አወድሶ ፣ ሟቾችን የሚከስ
ደንታ መቼ ሰጠው ፣ ሕዝብ እያሳዘነ ፣ ያልማል ለመንገሥ ።

የቤታችን ቀጋ ፣ የውጭ አልጋ ሆኖ ፣ አንጋች አጋፋሪ
የመንደር አውደልዳይ ፣ እየለቃቀመ ፣ ውራጅ ፍርፋሪ
ዲስኩር የሚያበዛ ፣ ባፉ ቅቤ ጠባሽ ፣ አስመስሎ አዳሪ
የተሙለጨለጨ ፣ የሚጨበጥ የለው ፣ የሆነ መሰሪ
መች ባቋም ይፀናል ፣ ለይምሰል ነው እንጂ ፣ ያጠለቀ ሱሪ
ስለማንነቱ ፣ ምስክር አያሻም ፣ ቃሉ ነው መስካሪ ።

ስለ ክፋቱ ጥግ ፣ ደፍሮ የጻፈ ሰው ፣ በሬ ሆይ እያለ
ሰው ገደል የሚጥል ፣ እንደወዳጅ ቀርቦ ፣ በአፍ እየደለለ
ጎሮሮው መቃብር ፣ አስመስሎ የሚያድር ፣ እየሸነገለ
ውስጡን ለቄስ አባይ ፣ በዘር በሃይማኖት ፣ እየከፋፈለ
ሕዝብ ፣ አፍዝ አደንግዝ ፣ እንደደገሙበት ፣ እየተከተለ
ቃልና ተግባሩ ፣ እንዳልተጣጣሙ ፣ የለም ያስተዋለ ።

እንኳን ዕውን ሆኖ ፣ ለአይምሮ የሚከብድ ፣ ሲያስቡት በምናብ
ፅላት ፣ ታቦት ደፍሮ ፣ ምዕመን የሚገድል ፣ ያበጠ በጥጋብ
መልኩን አሳምሮ ፣ የፋኝት ልጅ መርዛም ፣ ወርቅ መሳይ መዳብ
ታስሮለታል መሰል ፣ ከግራ ክንዱ ላይ ፣ የዲያቢሎስ ክታብ
በዕውር ድንብሩ ፣ በአብይ ጅንጀና ፣ ተጎትቶ እንዲሳብ
ባገር ላይ ጨልሞ ፣ ያልነበረው ገንኖ ፣ የመበተን ድባብ
ዛሬም አፈ ቅቤው ፣ ይነዳው አላጣም ፣ ሽንጋይ ፣ የሳር እባብ ።

ታዛቢው

February 18, 2020